**ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን)**

---

# ለሃይማኖት መሪዎችና ለኢትዮጵያ ማኅበረሰብ አመራሮች

በአሁኑ ጊዜ በአገራችን እየተካሄደ ባለው ጭቆና፣ ግድያ፣ አፈና፣ እስራት፣ ሥራ አጥነት፣ ወዘተ ምክንያት ከአገራችን እየኮበለሉ ወደተገኘው ቦታ ጥገኝነት ለማግኘት የሚሞክሩ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ መምጣቱ በቅርብ ጊዜ የተከሰቱትን ሁኔታዎች ግልጽ አመልካቾች ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህ ስደተኞች ጥገኝነት ለማግኘት በየአገሩ በሚከራተቱበት ጊዜ ከሚያስጠጋ ዘመድ ጀምሮ ምንም አለኝታ የሌላቸው በመሆኑ እጅግ መራራ የሆነ መከራን እየተቀበሉ ይገኛሉ፡፡ እኛ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ የምንገኝ ይህንን ደብዳቤ ለእናንተ የሃይማኖት መሪዎችና የማኅበረሰብ አመራሮች እንድንጽፍ ያስገደደን ዋነኛ ምክንያት ከማኅበረሰቡ ጋር ባላችሁ የቀረበ ግንኙነት ይህንን ችግር ተመለክክታችሁ የበኩላችሁን እንድታደርጉ ለማሳሰብ ነው፡፡

ይህንን የስደተኞች ጉዳይ አስመልክቶ ወደ ጋራ ንቅናቄያችን የሚላኩ መልዕክቶች በርካታ ሲሆኑ እነዚህን መልዕክቶች የሚጽፉት የእኛው ወገኖች የሆኑ እህቶቻችን፣ ወንድሞቻችን፣ ወዳጆቻችን፣ ቤተሰቦቻችን፣ በአጠቃላይ የእኛው ወገኖች ናቸው፡፡ መልእክቶቹም እንዲህ ይነበባሉ፡-

> *ውድ አባቴ፣ እናቴና ወንድሞቼ፣*
> *ከአዲስ አበባ ኢትዮጵያና ከእናንተ ተለይቼ መሄዴን ስነግራችሁ ከፍተኛ ሃዘንና ጸጸት ይሰማኛል፡፡ ይህንንም ውሳኔዬን ከመሄዴ በፊት ሳላሳውቃችሁ በመፈጸሜ በእውነት አዝናለሁ፡፡ የምወዳትን አገሬን ለቅቄ እንድወጣ ያደረገኝ ድህነት ወይም የኢኮኖሚ ጥገኝነት ሳይሆን በገዢው ፓርቲ (ህወሃት) ሃላፊዎች በተደጋጋሚ የደረሰብኝ ጥቃትና እንግልት ነው፡፡ በአገሬ ኢትዮጵያ ለመኖር ጠንካራ ፍላጎት ቢኖረኝም ነጻነት ማጣትና ለደኅንነቴ ዋስትና አለመኖር የምወዳትን አገሬን እንድለቅ አስገድደውኛል፡፡ በተደጋጋሚ የሚሰነዘርብኝ ማስፈራሪያና ዛቻ እየተቀበልኩ ለመኖር የማልችልበት ደረጃ ላይ በመድረሴ ነው ይህንን ልወስን የቻልኩት፡፡. . . ተወልጄ ባደኩባት አገር ስደተኛና እስረኛ ሆኜ የመኖር ያህል እየተሰማኝ በዚሁ መቀጠል ባለመቻሌ ነው ለእናንተ ቤተሰቦቼ ምንም ሳልነግር ነጻነቴን ከሌላ ቦታ ለማግኘት አገሬን ለቅቄ የወጣሁት . . . (ዳዊት ከኬንያ)*

ሕወሃት/ኢህአዴግን ያለማቋረጥ ላለፉት 20 ዓመታት ከታገሉት ብርቅዬ ጋዜጠኞቻችን መካከል በአሁኑ ጊዜ በስዊድንና ኖርዌይ የጥገኝነት ጥያቄው ውድቅ የተደረገበትና ወደ ኢትዮጵያ የመመለስ ግዴታ የተጣለበትን የወንድማችን አስናቀ መልዕክት ከኖርዌይ እንዲህ ይነበባል፡-

> *አሁን በኢትዮጵያ ያለው አገዛዝ የሚያደርሰው የሰብዓዊ መብት ረገጣ፣ ሃሳብን የመግለጽ ጭቆና፣ የመልካም አስተዳደር ዕጦት፣ ወዘተ ጉዳዮች ሲያሳስቡኝ የቆዩ ጉዳዮች ናቸው፡፡ እነዚህንም ተቃውሜ በመቆሜ ታስሬአለሁ፣ በአእምሮና በአካሌ ላይ የአገዛዙ የደኅንነት አባላት ከፍተኛ ጉዳት አድርሰውብኛል፡፡ በዋስ ከተፈታሁም በኋላ ላለፉት አራት ዓመታት ያላቋረጠ ክትትል ሲካሄድብኝ ቆይቷል. . .ጉዳዬንም ለፍርድቤት አቅርቤ ክሱ እንዲሰረዝና የዋስ ገንዘቤ እንዲመለስ ጠይቄ ነበር፡፡ ሆኖም ፍርድቤቱ ያቀረብኩትን ይግባኝ ውድቅ ሲያደርግ የአገዛዙ የደኅንነት ሰዎች እንደገና አስረውኛል፡፡ ቤተሰቤ በማይጠይቀኝ፣ ፍርድቤት ልቀርብ በማልችልበት፣ ምግብና ውሃ እንዳላገኝ ተከልክዬ ጨለማ ቤት ውስጥ ታስሬአለሁ፡፡ በዚህም ጊዜ የደኅንነት ሰዎች በኀማ ዱላ በተደጋጋሚ ደብድበውኛል. . .*

*የድኅረምረቃ ትምህርቴን ለመከታተል ከኢትዮጵያ ለማምለጥ የምችልበት አጋጣሚ ባገኝም በደረሰብኝ የስነልቦና ቀውስ ምክንያት ትምህርቴን ለመከታተል አልቻልኩም፡፡ . . . በህይወት ለመኖር ምንም ተስፋ የለኝም፡፡ እባካችሁን በፈጣሪ ስም እርዱኝ፤ እባካችሁን፡፡ (አስናቀ ከኖርዌይ)*

ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርነው እነዚህ ከሚደርሱ እጅግ በርካታ መልዕክቶች በጣም ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ወገኖቻችን በሰሜን አፍሪካ ይህ ነው የማይባል ሰቆቃ እየደረሰባቸው ይገኛል፡፡ ተመልሰው ወደ ኢትዮጵያ ከመሄድ ይልቅ ባሉበት ለመሞት በመቁረጥ በየዕለቱ ሞትን እየተጋፈጡ ይገኛሉ፡፡ ባለፈው ወር ወደ በቱኒሲያ ወደብ አድርጎ ወደ ጣልያን ይሄዳል በተባለ ኮንቴይነር ውስጥ የተደበቁ 70 ኢትዮጵያውያን ኮንቴይነሩን ያጓጉዝ የነበረው የጭነት መኪና ሊቢያ ላይ ሲበላሽ ሹፌሩ ጥሏቸው በመሄዱ ሁሉም አልቀዋል፡፡ ሌሎችም ወገኖቻችን በሌሎች አገሮች ከዚህ ያልተናነሰ መከራ እየደረሰባቸው የሰው ልጅ ሊሸከመው ይችላል ተብሎ የማይገመት ሰቆቃ እየተቀበሉ ይገኛሉ፡፡

በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያውያን በመካከለኛው ምስራቅ፣ በአፍሪካ፣ በእስያ፣ በደቡብና መካከለኛው አሜሪካ፣ በአውስትራሊያ፣ ወዘተ ይህ ነው የማይባል መከራ እየደረሰባቸው አንዳንዶችም እየሞቱ ይገኛሉ፡፡ የጋራ ንቅናቄያችንም የእነዚህን ወገኖቻችን ጉዳይ በሰማ ጊዜ ሁሉ ሲቻል በአካል እየተገኘን ካልሆነም ከአገራቱ ባለሥልጣናት ጋር በመጻጻፍ በጃፓን፣ በሜክሲኮ፣ በኖርዌይ፣ በባህሬይን፣ በሶሪያ፣ በጅቡቲ፣ በኬንያ፣ በዱባይ፣ በማልታ፣ በጣልያን፣ በሊቢያና በቱኒሲያ ያሉትን ስደተኞች ለመርዳትና ጉዳያቸው በተገቢው መንገድ እንዲታይ የበኩሉን ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ሆኖም ንቅናቄያችን በቅድሚያ ከቆመለት ዓላማ እንዲሁም ካለን የሰው ኃይልና የፋይናንስ አቅም አኳያ ህ ሁኔታ ከፍተኛ ተጽዕኖ እያሳደረብን ይገኛል፡፡ ስለዚህም ነው ጉዳዩን ወደእናንተ ልናመጣው የተገደድነው፡፡ የጋራ ንቅናቄያችን ለእነዚህ ሁሉ ችግሮች ቀዳሚ መንስዔ የሆነውንና ኢትዮጵያውያንን ለስደት እየዳረገ ያለው የአገዛዝ ሥርዓት የሚለወጥበትና ‹‹ከጎሣ ይልቅ ለሰብዓዊት ቅድሚያ›› የሚሰጥባት አዲሲቷ ኢትዮጵያ ትመሠረት ዘንድ ጥረቱን ቢቀጥልም ወገኖቻችን በእንደዚህ ዓይነት መከራ ሥር ሲወድቁ እያየንና እየሰማን ‹‹ይህ ጉዳይ ከንቅናቄያችን ዓላማ ጋር ተዛማጅነት የለውም›› ሳንል እንዳስፈላጊነቱ ያቅማችንን ስናደርግ ቆይተናል፡፡ አሁን ካለው ሁኔታ አኳያ ግን የእናንተ ድጋፍና በጉዳዩ ቀዳሚውን ስፍራ መያዝ ከመቼውም ይልቅ አስፈላጊ መሆኑን አምነንበታል፡፡

እንደሚታወቀው ሁሉ እናንተ የሃይማኖት ተቋማትም ሆናችሁ የኢትዮጵያ ማኅበረሰቦች ለበርካታ ኢትዮጵያውያን የመንፈሳዊ ምክር፣ የስደተኝነት ጉዳይ አገልግሎት፣ የገንዘብ ዕርዳታ፣ ወዘተ ስትለግሱ በርካታ ዓመታትን ማሳለፋችሁ ፈጽሞ የማይካድ ነው፡፡ ይህም ተግባራችሁ ከዕርዳታ ተቀባዩ ጋር የቀረበና የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖራችሁ ማድረጉ እሙን ነው፡፡ ስለዚህ አሁንም ራሳችሁን በእነዚህ በመከራና በስቃይ ላይ በሚገኙ ወገኖቻችን ቦታ ላይ በማስቀመጥ የእነርሱ ድካምና መከራ፣ስቃይና እንግልት እንድትመለከቱና እንድታጤኑት እንጠይቃችኋለን፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር ‹‹ሰው ሆይ÷ መልካሙን ነግሮሃል፤ እግዚአብሔርም ከአንተ ዘንድ የሚሻው ምንድር ነው? **ፍርድን ታደርግ ዘንድ÷** ምሕረትንም ትወድድ ዘንድ÷ ከአምላክህም ጋር በትሕትና ትሄድ ዘንድ አይደለምን?›› ይላል፡፡ (ሚክያስ 6፡8) በሌላ ቦታ ላይ ደግሞ የሌሎችን ጩኸት ላለመስማት ጆሮአችንን መድፈን የእኛ እንዳይሰማ እንደሚያደርግ ሲናገር **‹‹ሰው የድኾችን ጩኸት ላለመስማት ጆሮውን ቢዘጋ፤ እርሱም (በተራው) ይጮኻል፤ መልስም አያገኝም፡፡››** (ምሳሌ 21፡13)

በእስልምና ሃይማኖትም እንዲሁ በቅዱስ ቁርኣን ላይ ፍትሕን ማጓደል ፈጽሞ ተቀባይነት የሌለው ነገር እንደሆነ በበርካታ ቦታዎች የተጠቀሰ ሲሆን በተለይም ነብዩ መሐመድ (ሰአወ) በአንድ ወቅት ይህንን የመሰለ ምክር ሰጥተው ነበር **‹‹ጭከናን እና ኢፍትሐዊነትን ፈጽመው ከእናንተ ይወገዱ፤ ራሳችሁንም ከስስት ጠብቁ፤ እነዚህ በሙሉ ከእናንተ በፊት የነበሩ ሕዝቦች የመጥፊያ ምክንያቶች ሆነዋል፡፡››** (ሃዲት፤ 203) በሌሎች ሃይማኖቶችም ከዚህ ያልተናነሰ ጥቅስ

ማቅረብ ይቻላል፡፡ ፍትሕ እንዲሰፍን ማድረግ፣ ለተቸገረው መቆም፣ ለተበደሉት ድምጽ መሆን፣ ወዘተ የሃይማኖት ተቋማትም ሆኑ ማንኛውም በሰብዓዊ መብት ላይ ያተኮሩ ድርጅቶች ዋንኛ ዓላማ እንደሆነ ማንም የሚክደው አይደለም፡፡ ታዲያ እነዚህ ሁሉ ኢትዮጵያውያን በዓለም ዙሪያ በእንደዚህ ዓይነት አሰቃቂ ሁኔታ መከራ ሲቀበሉ የሃይማኖት ተቋማትና የኢትዮጵያ ማኅበረሰቦች የት ነው ያላችሁት? በእርግጥ እስካሁን በተለያየ መልኩ የምትችሉትን ስታደርጉና እርዳታችሁን ስትሰጡ እንደነበር እሙን ነው፤ለዚህም ምስጋና ይገባችኋል፡፡ ሆኖም ግን የችግሩ መጠን ከመቼም ይልቅ እየገዘፈ በመምጣቱ ነው ይህንን ጥሪ እንድናቀርብላችሁ የተገደድነው፡፡

ለእንደዚህ ዓይነቱ ሰብዓዊ ጥሪ ራስን ማነሳሳትና ሌሎችም እንዲተባበሩ ማድረግ ፈጣሪ የሚጠብቅብን ዋንኛ ተግባር ነው፡፡ ምክንያቱም ስንወለድ ጀምሮ የመኖር፣ የመምረጥ፣ የፈለግነውን የማድረግ፣ ወዘተ የማይገሰሱ መብቶች የሰጠን ራሱ ፈጣሪ ነውና፡፡ እነዚህ መብቶች በማንኛውም አገር መንግሥትም ሆነ ግለሰብ መሪ የሚለገሱ ወይም የሚነፈጉ አይደሉም፡፡ የፈጠረን አምላክ ያልነፈገንን የትኛው ፍጡር ነው ሊወስድብን ወይም ሊሸራርፍብን የሚችለው? ራሳችንን በማዋረድ ሎሌ ካላደረግን በስተቀር እነዚህን የከበሩ በማንም የማይጣሱና የማይገሰሱ መብቶች ማንም ሊነካቸው ፈጽሞ ሥልጣን የለውም፡፡ እነዚህም መብቶች እንዲከበሩ ጥያቄ ማቅረብም ሆነ እንዳይጣሱ ጥንቃቄ ማድረግ፤ እንዲሁም ጨካኞችና አምባገነኖች በጡንቻቸው ተማምነው እነዚህን መብቶች ሲጥሱና ፍትህን ሲያዛቡ ስናይ ‹‹ተዉ ይህ ተግባር ተገቢ አይደለም›› ማለት ፖለቲካዊ ሳይሆን አምላካዊ ተግባር ነው፡፡ አንድ የሃይማኖት ተቋም እነዚህን ጉዳዮች አንስቶ ዜጎች መብታቸው እንዲከበርና በአገራቸው ነጻነታቸውን ያለገደብ እንዲለማመዱ መንግሥታትን መጠየቅና መሪዎችን መገሰጽ ካልቻለ አስራትንና መባን እየሰበሰበ ህንጻውንና መጎናጸፊያውን እያሳመረ የሚኖር በምድር ኑሮው የረካ ዓለማዊ ተቋም ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ በአሁኑ ጊዜ ከበርካታ የሃይማኖት መሪዎች እንደሚሰማው ሳይሆን ‹‹ይህ ፖለቲካ አይደለም የሰብዓዊ መብት ጉዳይ ነው›› በማለት ለዚህ የተቀደሰ ዓላማ ከጥንት ጀምሮ እስከዘመናችን ድረስ በታማኝነት የቆሙ በርካታ የሃይማኖት መሪዎች ከሁሉም ሃይማኖቶች መጥቀስ ይቻላል፡፡ ነብዩ አሞጽ፣ መጥምቁ ዮሐንስ (ሄሮድስ የወንድሙን ሚስት ማግባቱን በመቃወሙ የተሰየፈ)፣ አቡነ ጴጥሮስ (የኢትዮጵያ ሕዝብ ለጣሊያን እንዳይገዛ የገዘቱ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ጳጳስ)፣ መሃትማ ጋንዲ (ከሂንዱ እምነት መሪ)፣ ዶ/ር ኪንግ (የፕሮቴስታን እምነት መሪ - ሬቨረንድ)፣ አልሃጅ ማሊክ አል ሻባዝ (ማልኮም ኤክስ)፣ ወዘተ፡፡

ስለዚህ በማያቋርጥ ስቃይና መከራ ውስጥ ለሚገኘው ሕዝባችን የሃይማኖት ተቋማትና የማኅበረሰብ መሪዎች በአንድነት በመሆን ድምጻቸውን እንዲሰሙ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡ በስደት በየአገሩ እየተንከራተቱ ያሉትን ወገኖቻችንን ከጸሎት ባለፈ መልኩ በተግባር ለመርዳት እንድትችሉና የችግሩ ሥረመሠረት መፍትሔ የሚያገኝበትን መንገድም እንድትቀይሱ ፈጣሪ ይርዳችሁ፡፡ ለነፍሳቸሁ በማደር ለምታስተምሩት ትምህርት በታማኝነት እንደምትቆሙት ሁሉ ይህንንም የአገራችንን ጉዳይ ቀዳሚ በማድረግ በየአገሩ ለሚንከራተቱት ወገኖቻችንም ሆነ በአጠቃላይ ለአገራችን መፍትሔ ማምጣት ትችሉ ዘንድ ርህሩህና መሐሪው አምላክ ይርዳችሁ፡፡ ውጤቱንም በተስፋ እንጠብቃለን፡፡

ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን)

********************************************************************

ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ መረጃ ዋና ዳይሬክተሩን ለአቶ ኦባንግ ሜቶ (obang@solidaritymovement.org) በመጻፍ ወይም በስልክ (202) 725 - 1616 በመደወል ወይም ድረገጻችንን (www.solidaritymovement.org) በመጎብኘት ለመረዳት ይችላሉ፡፡

